*Amharic*



# ሁሉም፡ሴቶች፡ስለ፡ የማህፀን፡በር፡ ቅድመ፡ካንሰር፡ ምርመራ፡ (Pap tests) ማወቅ፡አለባቸው።

*የማህፀን፡በር፡ቅድመ÷ካንሰር፡ምርመራ፡ የአንገተ÷ማህፀንን፡ (Cervical) ካንሰር፡ያስቀራልና፡ለምርመራዎ፡ ዛሬውኑ፡ቀጠሮ፡ይያዙ።*

በማኒቶባ
የአንገተ÷ማህፀን
ካንሰር
ምርመራ
መረሃ፡ግብር

MANITOBA CERVICAL CANCER SCREENING PROGRAM

CancerCare MANITOBA
*Action Cancer Manitoba*

*All translated materials completed in partnership with Sexuality Education Resource Centre*

## የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡ምንድነው?

*የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡በአንገተ+ማህፀን፡ላይ፡የሚገኘውን፡ለውጥ፡የሚመረምር፡ሲሆን፡ቅድመ፡ለውጦችን፡ማከም፡ደግሞ፡የአንገተ+ማህፀንን፡ካንሰር፡ሊየስቀር፡ይችላል።*

## አንገተ+ማህፀን፡ምንድነው?

*አንገተ፡ማህፀን፡ክፍተት፡ያለውና፡ከማህፀን፡ጫፍ፡ላይ፡የሚገኝ፡ሲሆን፡ህፃናት፡ሲወለዱ፡የሚወጡት፡በእዚሁ፡በአንገተ፡ማህፀን፡ውስጥ፡ነው።*

## የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡ለእኔ፡ያስፈልገኛልን?

*ፍትወተ፡ስጋ፡ፈጽመው፡ከሆነ፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡ያስፈልጎታል።*

## በየስንት፡ጊዜ፡ነው፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራን፡የማደርገው?

*አብዛኛዎቹ፡ሴቶች፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራን፡ለሦስት፡አመት፡በየአመቱ፡አንድጊዜ፡ማድረግ፡ይገባቸዋል።የእዚህ፡ምርመር፡ውጤት፡ጥሩ፡ከሆነ፡በኋላ፡በየሁለት፡አመት፡አንድ፡ጊዜ፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡ማድረግ፡ይገባቸዋል።በበለጠ፡ሃኪሞዎን፡ወይም፡ነርሶዎን፡ቢያማክሩ፡የተሻለ፡ይሆናል።*

## የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡በግብረ፡ስጋ፡ግንኙነት፡ለሚመጣ፡በሽታ፡ይመረምራልን?

*አይመረምርም። በሽታው፡ይኖርብኛል፡ብለው፡ከተጠራጠሩ፡ሃኪሞዎን፡ወይም፡ነርሶዎን፡ያማክሩ።*

## ማህፀኔ፡በቀዶ፡ጥገና፡የወጣ፡ከሆነ፡ለእኔ፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡ያስፈልኛልን?

*ምናልባት፡የሚያስፋልጎዎት፡ከሆነ፡ሃኪሞዎን፡ወይም፡ነርሶዎን፡ያማክሩ።*

## ያረጥኩ፡ከሆነ፡ለእኔ፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራ፡ያሰፈልገኛልን?

*አዎን፡ያስፈልጎታል።*

## መቼ፡ነው፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራዬ፡የሚያበቃው?

*እድሜዎ፡ሰባ፡አመት፡ሲደርስ፡ምናልባት፡ምርመራው፡ሊያበቃ፡ይችላል።ሃኪሞዎን፡ወይም፡ነርሶዎን፡ያማክሩ።*

## የመጨረሻው፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራዬ፡መቼ፡ነበር?

*የመጨረሻው፡የማህፀን፡በር፡ቅድመ+ካንሰር፡ምርመራዎ፡መቼ፡እንደ፡ነበር፡ማስታወስ፡ካልቻሉ፡በስልክ፡ቁጥር፡204-788-8626 ወይም፡በነፃ፡መስመር፡ 1-866-616-8805 ወይም፡ሃኪሞዎ፡ዘንድ፡ይደውሉ።*

## ስለ፡አንገተ፡ማህፀን፡ካንሰር፡ምርመራ፡የበለጠ፡ለማወቅና፡ለመረዳት፡የምችለው፡የት፡ነው?

*በስልክ፡ቁጥር፡204-788-8626 ወይም፡በነፃ፡መስመር፡1-866-616-8805 በማኒቶባ፡የአንገተ+ማህፀን፡ካንሰር፡ምርመራ፡መረሃ፡ግብር፡ዘንድ፡ይደውሉ።*

www.cancercare.mb.ca/MCCSP *ወይም፡*